**Español:** masspowerchoice.com/cambridge/letter_spanish.pdf
**Kreyòl ayisyen:** masspowerchoice.com/cambridge/letter_hcreole.pdf
**বাংলা:** masspowerchoice.com/cambridge/letter_bangla.pdf
**አማርኛ:** masspowerchoice.com/cambridge/letter_amharic.pdf
masspowerchoice.com/cambridge/letter_arabic.pdf **:عربي**

# የካምብሪጅ ከተማ

የማሕበረሰብ የሙብራት/ኤሌክትሪክ ቅንብር ፕሮግራም
(COMMUNITY ELECTRICITY AGGREGATION PROGRAM)
**የማስታወቅያ ደብዳቤ**

ታህሳስ 8 ቀን 2021

የተከበራችሁ የካምብሪጅ ነዋሪዎች ወይም የንግድ ስራ ባለቤቶች፡

ይህ ደብዳቤ የሙብራት ክፍያዎን በሚመለከት አስፈላጊ መረጃዎችን የያዘ ነው።

በአሁኑ ወቅት ፡ ኤቨርሶርስ ቤዚክ አገልግሎት (Eversource Basic Service) በሚባል የሙብራት/የኤሌክትሪክ አገልግሎት ነው በመገልገል ላይ የሚገኙት። ይህም ማለት የሙብራት/ኤሌክትሪክ አገልግሎት የሚያገኙት ኤቨርሶርስ((Eversource) ከሚባለው የኤሌክትሪክ ተቋም ነው። ይሄው ተቋም መብራት እንዲደርሶት ያደርጋል። አሱም ነው መብራት ወይም ኤሌትሪክ ከሌሎች የሚገዛሎት ማለት ነው።

ይሁንና የካምብሪጅ ከተማ፡ **የካምብሪጅ የማሕበረሰብ የሙብራት/ኤሌክትሪክ ቅንበር ፕሮግራም** (Cambridge Community Electricity Program )የሚባል የሙብራት ፕሮግራም አለው። በዚህ ፕሮግራም፡ ኤቨርሶርስ (Eversource)ኤሌክትሪክ ያስተላለፍሎታል፤ ከተማው ግን የራሱን የኤሌክትሪክ አቀባይ መምረጥ ይፈልጋል። ከተማው: ይህንን ፕሮግራም፡ ከጸሃይ የሚገኝ አዲስ የኤሌክትሪክ ሃይል በካምብሪጅ ውስጥ ለማስፋፋት አየተጠቀመበት ነው። በዚህ ፕሮግራም ውስጥ በመሳተፍ እርስዎም: ይህ አዲስ የኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጭያ ባለው የኤሌክትሪክ ሃይል ላይ እንዲጨመር በማድረግ በኩል ያግዛሉ ማለት ነው፤

**ይህ ደብዳቤ ከደረሶት በውሃላ፡ ምንም ነገር ካላደረጉ ፡ በካምብሪጅ ማሕበረሰብ የኤሌክትሪክ ፕሮግራም (Cambridge Community Electricity program) ውስጥ በቀጥታ ይገባሉ።**

**በፕሮግራሙ ውስጥ በቀጥታ እንዲገቡ ከመደረግዎ በፊት፤ መግባት እንደማይፈልጉ የሚያሳይ ጥያቄዎን የያዘ ደብዳቤ ከጥር 10 ቀን 2022 በፊት ፖስታ ቤት እንዳስገቡት የሚያሳይ ምልክት የያዘ መሆን አለበት።**

**በፕሮግራሙ መሳተፍ ማለት**: ኤቨርሶርስ (Eversource) የኤሌክትሪክ ሰጪዎ ሆኖ ይቀጥላል፤ ለኤሌክትሪክ (ለሙብራት)የሚከፍሉት የክፍሊት ወረቀትም ከእነሱ ይመጣሎታል። መብራት ቢቋረጥቦትም የሚደውሉት ለእነሱ ነው፤ ግን በዚሁ በኤቨርሶርስ (Eversource) የኤሌክትሪክ ክፍሊት ወረቀት ላይ ዳይሬክት ኤነርጂ (Direct Energy) የሚል ስም በአቅራቢ ዝርዝር ላይ ተመዝግቦ ያያሉ። የካምብሪጅ ማህበረሰብ የኤሌክትሪክ ፕሮግራም (Cambridge Community Electricity program) ዋጋም ኤሌክትሪክ ወደእርሶ ጋ እንዲደርስ የሚያስችል ክፍያን ያንጸባርቃል።

**አነስተኛ ገቢ ላላቸው ሰዎች የሚደረግ የአቅርቦት መጠንና የነዳጅ እገዛ ለማግኘት ብቁ ሆነው ተገኝተው ከነበሩ፡ አነኝያኑ ጠቀሜታዎችን ማግኘትዎን ይቀጥላሉ። በዛው ሲደረግሎት በቆየው የአገዛ መጠን ይቀጥላሉ።**

**ላለመሳተፍ መምረጥ ማለት፡** ኤቨርሶርስ( Eversource) የኤሌክትሪክ አቅራቢዎ ሆኖ ይቀጥላል፡ አቅርቦቱን በተመለከተ ያለው የክፍያው ከፊል አካልም እንደነበረበት በኤቨርሶርስ( Eversource) የዋጋ መጠን ይቀጥላል ማለት ነው።

## የመሳተፍ ጠቀሜታ

**የከተማው፡ የሚታደስ ኤሌክትሪክ** - ኤሌክትሪኮ፡ አንዴ ከጀመረ በውሃላ፡ ከከተማው ከጸሃይ ብርሃን ከሚገኘው አዲስ የሃይል ፕሮጀክት ተቋዳሽ ይሆናል፤ ውጤቱም ኤሌክትሪኮ ክፍለሃገሮ፡ በአነስተኛ ደረጃ ከሚጠይቀው በላይ የሚታደስ የኤሌክትሪክ ሃይል ያገኛል ማለት ነው።

**ምርጫ** - ፕሮግራሙ ሁለት ምርጫዎችን ይሰጦታል፡ 1)ስታንዳርድ ግሪን (Standard Green) በካምብሪጅ ካለው ከጸሃይ ብርሃን የሚገኘውን አዲስ የሚታደስ ሃይል የሚያጠቃልል 2) 100% ግሪን ፕላስ (Green Plus) 100% የሚታደስ የኤሌክትሪክ ሃይልና በካምብሪጅ ያለው ከጸሃይ ብርሃን ከሚገኘው የኤሌክቲክ ሃይል። በ ስታንዳርድ ግሪን (Standard Green ) ውስጥ ወድያውኑ ይገባሉ፤ ከፈለጉ ግን 100% ግሪን ፕላስ( Green Plus) ሊመርጡ ይችላሉ፡ (ዝርዝር መረጃ ከበስተውሃላ ይገኛል)።

**ሊገኝ የሚችል የዋጋ ቅነሳ** - የፕሮግራሙ ዋጋ ፡ከኤቨርሶርስ መሰረታዊ የአገልግሎት ዋጋ ( Eversource's Basic Service) ዝቅ ሊል ይችላል፤ ግን የኤቨርሶርስ መሰረታዊ የአገልግሎት ዋጋ ( Eversource's Basic Service) የመኖርያ ቤቶችንና አነስተኛ የንግድ ቤቶችን በተመለከተ በየስድስት ወሩ፡ ትላልቅ የንግድ ስራዎችን በተመለከተ ደግሞ በየሶስት ወሩ ይቀየራል።ይህም በመሆኑ የፕሮግራሙ ዋጋ ከኤቨርሶርስ( Eversource)ዋጋ በታች ሊሄድ አይችልም ይሆናል፡ ገንዘብ ለመቆጠብም ይቻላል ብሎ ዋስትና ለመስጠት አይቻልም።

* የስታንዳርድ ግሪን (Standard Green) ዋጋና የ100% ግሪን (Green) ዋጋ ሁለቱም በየአንዳንዱ ኪሎዋት የ$0.00075

## የካምብሪጅ ማህበረሰብ የ ኤሌክትሪክ ፕሮግራም

(Cambridge Community Electricity Program)

አዲሱ የሙብራት አገልግሎት ክፍያ

**10.20 ¢/kWh**

የኤቨርሶርስ (Eversource) የመኖርያ ቤቶች መሰረታዊ አገልግሎት

**15.735 ¢/kWh**

ንግድ ቤቶችን በሚመለከት የኤቨርሶርስ (Eversource) ዋጋ ከበስተጀርባ ይገኛል ▶

## የደንበኞች አገልግሎት

**1-844-379-9934**

## መሳተፍ አይፈልጉም?

**መሳተፍ ካልፈለጉ፡ ግዴታ የለቦትም ፤ ከፕሮግራሙ ለመውጣት የሚከፍሉት መቀጮ ወይም ገንዘብ የለም፡ ባፈለጉበት ግዜ ከፕሮግራሙ ሊወጡ ይችላሉ።**

ላለመሳተፍ ከመረጡ፡ በኤቨርሶርስ(Eversource) መሰረታዊ አገልግሎት ደንበኛ ሆነው ይቀጥላሉ።

ከመግባትዎ በፊት ለመውጣት ከፈለጉ
**ከጥር 10 ቀን 2022** በፊት ከሚከተሉት ውስጥ አንዱን ያድርጉ፤

▶ ተያይዞ የተላከሎትን ካርድ ፈርመው (**ከጥር 10 ቀን 2022** በፊት) ይላኩ ወይም በስልክ ቁጥር **1-844-379-9934** ወደ ደንበኛ አገልግሎት ይደውሉ ወይም ኦንላይን ወደ **masspowerchoice.com/cambridge** ገብተው ከፕሮግራሙ ይውጡ።

ወደፊት ለመውጣት ከፈለጉ ከሚከተለው ውስጥ አንዱን ያድረጉ፡

▶ ወደ ደንበኞች መስመር በስልክ ቁጥር **1-844-379-9934** በመደውል ወይም በኦንላይን **masspowerchoice.com/cambridge** በመግባት ሊወጡ ይችላሉ፤

## የፕሮግራሙ አማራጮችና ዋጋዎች

| 1. ምንም ካላደረጉ፡ በስታንዳርድ ግሪን( STANDARD GREEN) ይገባሉ፤ | **10.20 ¢/kWh*** ለመኖርያ ቤቶች፣ ትልላቅና ትናንሽ ንግድ ቤቶች (ይህ ከሁሉም ያነሰ የዋጋ ምርጫ ነው) |
|---|---|
| **የሚታደስ የኤሌክትሪክ ሃይል ይዘት** | ይህ የማሳቹሴትስ አነስተኛውን የሚታደስ የኤሌክትሪክ ሃይል ጥያቄን የሚያሙዋላ ሆኖ አንዴ ስራው ተጠናቆ መስራት እስከጀመረ ድረስ አዲሱ ከጸሃይ የሚገኘው የካምብሪጅ የሚታደስ ሃይል በተጨማሪ ይኖረዋል** |
| **የዋጋ እርዝማኔ ግዜ** | ምዝገባ- ጥር 2021 ሜትር ይነበባል |
| **የሚያልቅበት ግዜ** | በማንኛውም ግዜ መውጣት ይችላሉ፡ የመውጣት ክፍያ የለም |

| 2. 100%የሚታደስ የመብራት ሃይል ከፈለጉ 100% ግሪን ፕላስን GREEN *PLUS* መምረጥ ይችላሉ። ▶ 100% ግሪን ፕላስ( GREEN *PLUS* )ን ከመረጡ በስልክ ቁጥር 1-844-379-9934 ወደ ደንበኞች እገዛ መስመር ይደውሉ። | **13.669 ¢/kWh*** ለመኖርያ ቤቶች፣ ትልላቅና ትናንሽ ንግድ ቤቶች (ይህ በጣም ውዱ ምርጫ ነው) |
|---|---|
| **የሚታደስ የኤሌክትሪክ ሃይል ይዘት** | በኒው ኢንግላንድ (New England) ካሉት የሚታደሱ የኤሌክትሪክ ሃይሎች የሚገኝ 100% ንጹህ የኤሌክትሪክ ሃይል። ከጸሃይ ከሚገኘው የካምብሪጅ አዲስ ፕሮግራም፡ አንዴ ስራ ከጀመረ በውሃላ ተጨማሪ የሚታደስ ኤሌክትሪክ ያሰራጫል።** |
| **የዋጋ እርዝማኔ ግዜ** | ምዝገባ - ጥር ወር 2021 መለኪያ የተነበበት ወቅት |
| **የሚያልቅበት ግዜ** | ባፈለጉበት ግዜ መውጣት ይችላሉ፡ ለመውጣት የሚከፍሉት ገንዘብ የለም። |

| 3. ለመካፈል ካልፈለጉ በኤቨርሶርስ መሰረታዊ አገልግሎት (EVERSOURCE BASIC SERVICE) ውስጥ ይቆያሉ። | **15.735 ¢/kWh** መኖርያ ቤቶች<br>**14.732 ¢/kWh** አነስተኛ የንግድ ቤቶች<br>**27.543 ¢/kWh** ትላልቅ የንግድ ቤቶች |
|---|---|
| **የሚታደስ የኤሌክትሪክ ሃይል ይዘት** | ይህ የሚታደስ የኤሌክትሪክ/መብራት ሃይል ጥያቄን የማሳቹሴትስ ክፍለሃገር የሚጠይቀውን አንስተኛውን ዋጋ ያሙዋላል። |
| **የዋጋ እርዝማኔ ግዜ** | ከጥር 1 ቀን 2022 - ሰኔ 30 ቀን 2022- ለመኖርያ ቤቶችና ትናንሽ የንግድ ቤቶች ሂሳብ። ከ ጥር 1ቀን 2022 - መጋቢት 31 ቀን 2022 ለትላልቅ ንግድ ቤቶች ሂሳብ። የኤቨርሶርስ (Eversource) ለመኖርያ ቤቶችና ትናንሽ የንግድ ቤቶች የተመደበው የመሰረታዊ አገልግሎት ክፍያ በየ 6 ወሩ፤ ለትላልቅ ንግድ ቤቶች ደግሞ በየ 3 ወሩ ይቀየራል። |
| **የሚያልቅበት ግዜ** | ምንም ዓይነት የመውጣት ክፍያ ሳይጠየቁ ባፈለጉበት ግዜ መውጣት ይችላሉ። ይሁንና ትላልቅ ሲ&አይ (C&I) ዋጋቸው ጂ-3 (G-3)፣ ቲ-2 (T-2) እና ደብሊው-አር (WR) የሆነና የመንገድ መብራት እንዲደርግላቸው የሚጠይቁ በተመደበው መሰረታዊ ክፍያ ውስጥ ያሉ ደንበኞች፣የአገልግሎት ዋጋ በብድር መልክ ወይም በካሽ እንዲከፍሉ ይጠየቁ ይሆናል። |

* የአስተዳደር ክፍያ ሊኖርውና ለአንድ ኪሎዋት $0.002 የሚታሰብ የስራ ክፍያ አለው። በስምምነቱ ወቅት፡ የፕሮግራሙ ክፍያ፤ በአንዳንድ ህጎች ለውጥ ምክንያት፡ ወደላይ ከፍ ሊል ይችላል።

** ለስራ ተብሎ የሚሰበሰበው የክፍያ ገንዘብ ከጸሃይ የሚገኝ አዲስ የኤሌክትሪክ ሃይልን በማጎልበት ስራ ላይ ይውላል፤ ይሄው ስራ ሲጠናቀቅና ስራ ሲጀምር፡ከተማው በዚህ ፕሮጀክት የተሰበሰውን ገንዘብ በሳታንዳርድ ግሪን( Standard Green)ና በ100% ግሪን ፕላስ (Green Plus) የኤሌክትሪክ ተጠቃሚዎች ጥቅም ላይ ይውላል።

## በብዛት የሚጠየቁ ጥያቄዎች

**እዚህ ላይ ገንዘብ የመቆጠብ ዋስትና አለን?** የለም። ምን ዓይነት ደንበኛ እንደሆኑ ከታወቀ በኋላ፤ የኢቨርሶርስ (Eversource) የተመደበው መሰረታዊ የአገልግሎት ክፍያ በየስድስት ወሩ ወይም ከዛ ባነሰ ግዜ ውስጥ ይቀየራል፤ ወደፊት ደግሞ ምን ያህል እንደሚከፈል አይታወቅም። ስለዚህ የሚቀጥለው የኤቨርሶርስ (Eversource) የክፍያ መጠን ሓምሌ 1ቀን 2022- ለመኖርያ ቤቶችና ትናንሽ ንግድ ቤቶች፤ ሚያዝያ 1 ቀን 2022 ደግሞ ለትላልቅ ንግድ ቤቶች ይቀየራል። በወቅቱ ያለው የክፍያ መጠን ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ ከፈለጉ ወደ https://www.eversource.com ይግቡና ይመልከቱ።

**ከ ሌላ የኤሌክትሪክ ተቋም ጋር ስምምነት ፈርሜአለሁ፤ ምን ላድርግ?** ሌላ የኤሌክትሪክ ተቋም ካሎትና ከዚሁ ተቋም ጋር መቀጠል ከፈለጉ፡ ከካምብሪጅ ማህበረሰብ የኤሌክትሪክ ፕሮግራም መውጣት አለቦት። ይህንን ካላደረጉ ወይም መውጣትዎን ካልገለጹና ካልወጡ፡ በቀጥታ በፕሮግራሙ ውስጥ እንደገቡ ይቆጠራል፡ ካሎት የኤሌክትሪክ ተቋም ደግሞ ቅጣት ሊያስከትልቦት ይችላል።

**ከግብር-ነፃ አካውንት አለኝ። የአካውንቴን ከግብር-ነፃ የመሆኑን ሁኔታ እንዴት ማቆየት እችላለሁ?** እንደ የፕሮግራም ክፍሉ የሀይል አቅርቦት ዋጋ የግብር ክፍያ ይጠየቃል። ደንበኞች ተገቢውን የቀጥታ ሀይል (Direct Energy) ከግብር-ነፃ የመሆን መረጃ በማቅረብ ከማንኛውም ግብር መሰብሰብ ነፃ ለመሆን የመለየት እና የመጠየቅ ሀላፊነት አለባቸው። ዶክመንትዎን የት ላይ እንደሚያስረክቡ መረጃ ለማግኘት MassPowerChoice.com/Cambridge ይጎብኙ።

ሌላ ተጨማሪ ጥያቄዎች ካሎት እባክዎን ከ ደንበኞች አገዛ ክፍል አባሎች (customer support ),ጋር በስልክ ቁጥር **1-844-379-9934** ደውለው ተገናኙ ወይም ወደ **cambridge@masspowerchoice.com** ይጻፉ ወይም በኢንተርኔት ወደ **www.masspowerchoice.com/cambridge** ይግቡ፤ የፕሮግራማችን አማካሪዎች እርስዎን ለመርዳት ዝግጁዎች ናቸው።

ሉዊ ደፓስኬል (Louis DePasquale)
የከተማ አስተዳዳሪ

# የካምብሪጅ ማህበረሰብ ኤሌክትሪክ ፕሮግራም

X ______________________________________________

ፊርማ ቀን

## የመውጫ መመርያዎች

በካምብሪጅ ማህበረሰብ የኤሌክትሪክ ፕሮግራም ውስጥ ለመሳተፍ ከፈለጉ ምንም አይነት እርምጃዎችን መውሰድ አይኖርቦትም።

**በፕሮግራሙ መሳተፍ ካልፈለጉ ሊወጡ ይችላሉ።** መውጣት እንደሚፈለጉ ደብዳቤ ጽፈው በፖስታ መላክ ከፈለጉ፤

1. **በዚህ ካርድ ላይ ቀኑን ጽፈው ይፈርሙ**
2. **ካርዱን በተካተተው ፖስታ ውስጥ ያሽጉ**
3. **ፖስታውን በፖስታ ቤት በኩል ይላኩ**

ይህ ካርድ፤ በካርዱ ላይ ስሙ ተጽፎ በሚገኘው የመዝገብ ቤት ሹም መፈረም አለበት። በቀጥታ መመዝገብን ለማስወገድ ደብዳቤዎ ከ **ጥር 10 ቀን 2022** በፊት ፖስታ ቤት እንደገባ የሚያሳይ ምልክት በላዩ ላይ የተጻፈበት መሆን አለበት። በማንኛውም ግዜ መውጣት ከፈለጉ ወደ masspowerchoice.com/cambridge በመግባት ወይም ወደ ደንበኞች አገልግሎት ክፍል በስልክ ቁጥር 1-844-379-9934 በመደወል መውጣት ይችላሉ።